# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት
## ስለማሻሻያ ሞሽን አቀራረብ
## የወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2000 ዓ.ም

### አንቀጽ 1
### አውጪው አካል

የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ በምክር ቤቱ የአሰራርና የአባላት ስነ ምግባር ደንብ ቁጥር 3/1998 ዓ.ም. አንቀጽ 143 ንኡስ አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 191 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### አንቀጽ 2
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ስለማሻሻያ ሞሽን አቀራረብ የወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2000 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 3
### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ምክር ቤት" ማለት የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።
2. "ደንብ" ማለት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የአሰራርና የአባላት ስነ ምግባር ደንብ ቁጥር 3/1998 ዓ.ም ነው፡፡
3. "አፈጉባኤ" ማለት የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ ነው፡፡
4. "አባል" ማለት የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ነው፡፡

### አንቀጽ 4
### የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለምክር ቤቱ በሚቀርብ ማንኛውም ሞሽን፣ ወይም ረቂቅ ውሳኔ ወይም ረቂቅ ህግ ወይም የኮሚቴ ሪፖርትና ውሳኔ ሀሳብ ላይ በሚቀርብ የማሻሻያ ሞሽን እና ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

### አንቀጽ 5
### ዓላማ

በምክር ቤቱ የተለያዩ ሃሳቦች የሚንሸራሸሩበትና አባላት ሃሳባቸውን የሚገልጹበት ዴሞክራሲያዊ መድረክ የሚፈጠርበት ግልጽ አሰራር እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ 6**

**አተረጓጎም**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የሚፈጠር ክፍተት በደንቡ አንቀጽ 3 መሰረት እንዲሞላ ይደረጋል።

**አንቀጽ 7**

**ስለማሻሻያ ሞሽን**

1. ማንኛውም የምክር ቤት አባል ወይም የፓርላማ ቡድን፣

   ሀ/ የአፈ ጉባኤውን ፈቃድ በማግኘት ለም/ቤቱ ውይይት በቀረበ መሰረታዊ ሞሽን፣

   ለ/ ለምክር ቤቱ በቀረበ ረቂቅ ህግና የኮሚቴ ሪፖርት እና ውሳኔ ሃሳብ፣

   ሐ/ ለምክር ቤቱ በቀረበ ረቂቅ ውሳኔ ወይም ሪዞሉሽን ላይ በደንቡና በዚህ መመሪያ መሰረት የማሻሻያ ሞሽን ለማቅረብ ይችላል።

2. ማንኛውም የሞሽን ህግ እና ልማዳዊ አሰራር ለምክር ቤቱ በሚቀርብ የማሻሻያ ሞሽን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

3. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ የማሻሻያ ሞሽን በመሰረታዊ ሞሽኑ፣ በረቂቅ ህጉ ወይም በረቂቅ ውሳኔው ወይም በኮሚቴ ሪፖርትና ውሳኔ ሀሳብ ውስጥ የተካተተ ቃል፣ ሀረግ፡ ዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ፣

   ሀ/ እንዲወጣ፣

   ለ/ ተሰርዞ በሌላ እንዲተካ ወይም

   ሐ/ አዲስ እንዲጨመር የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል።

**አንቀጽ 8**

**የማሻሻያ ሞሽን ጠቅላላ መመዘኛ**

በደንቡ አንቀጽ 41 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ማንኛውም የማሻሻያ ሞሽን፣

1. ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆን አለበት፣
2. የቀረበውን ጉዳይ ወሰኑ የማያሰፋ መሆን አለበት፣
3. የቀረበውን ጉዳይ የበለጠ ግልጽ የሚያደርግ መሆን አለበት፣
4. አዲስ ጉዳይ እንዲካተት የማይጠይቅ መሆን አለበት፣
5. የቀረበውን ዋና ጉዳይ ትርጉም የማያሳጣ ወይም ቋንቋውን የማያዛባና ከዋናው ጉዳይ ጋር ተጣጥሞ ሊገባ በሚችል ሁኔታ መዘጋጀት አለበት።
6. መሠረታዊ ሞሽን፣ ረቂቅ ህግ ወይም ረቂቅ ውሳኔ በሙሉ ሰርዞ በሌላ የሚተካ መሆን የለበትም፣
7. ምክር ቤቱ ቀደም ሲል ካሳለፈው ውሳኔ ጋር የሚጋጭ መሆን የለበትም።

## አንቀጽ 9
## ስለማሻሻያ ሞሽን አቀራረብ

1. ማንኛውም የማሻሻያ ሞሽን አቅራቢ፤ እንዲሻሻል የሚጠይቀውን ጉዳይ በጽሁፍ አዘጋጅቶ ስሙንና ፊርማውን በማስፈር ለአፈጉባኤው ማቅረብ አለበት።
2. አቅራቢው በሞሽኑ፣ በረቂቅ ህጉ ወይም በረቂቅ ውሳኔው በኮሚቴው ሪፖርትና ውሳኔ ሀሳብ ውስጥ እንዲሰረዝ፣ እንዲተካ፣ እንዲወጣ ወይም እንዲጨመር የሚፈልገውን ቃል፣ ሀረግ፣ አረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ ቦታ በግልጽ ማመላከት አለበት።
3. አፈጉባኤው ከቀረቡለት የማሻሻያ ሞሽን ውስጥ መመዘኛውን ያሟሉትን በመለየት እንደጉዳዩ ቅደም ተከተል ለምክር ቤቱ እንዲቀርብ ያደርጋል።
4. የአፈጉባኤውን ፈቃድ ያገኘ ማሻሻያ ሞሽን በቅደም ተከተል ዝርዝር ተዘጋጅቶ እና ተራ ቁጥር ተሰጥቶት ከምክር ቤቱ አጀንዳ ጋር ለአባላት እንዲደርስ ይደረጋል።
5. የማሻሻያ ሞሽን ከአንድ በላይ በሆኑ አባላት የቀረበ እንደሆነ ስሙ በመጀመሪያው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው አባል የ"እነ----" ማሻሻያ ተብሎ ሊቀርብ ይችላል።

## አንቀጽ 10
## የማሻሻያ ሞሽን የማቅረቢያ ጊዜ

1. በመሰረታዊ ሞሽን ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ሞሽኑ ተቀባይነት አግኝቶ በማስታወቂያ ሰሌዳ ከወጣበት ወይም በአጀንዳ ተቀርጾ ከተሰራጨበት ጊዜ ጀምሮ ም/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የሚያደርገው ስብሰባ ከመጀመሩ ከ30 ደቂቃ በፊት ሊቀርብ ይችላል።
2. በረቂቅ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ረቂቅ ውሳኔው በአጀንዳ ተቀርጾ ከተሰራጨበት ጊዜ ጀምሮ ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ የሚያደርገው ስብሰባ ከመጀመሩ ከ30 ደቂቃ በፊት ሊቀርብ ይችላል።
3. በረቂቅ ህግ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ረቂቅ ህጉ ለምክር ቤቱ የመጀመሪያ ንባብ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ንባብ እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ሊቀርብ ይችላል።
4. በኮሚቴ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ የውሳኔ ሃሳቡ በአጀንዳ ተቀርጾ ለአባላት ከተሰራጨበት ጊዜ ጀምሮ ኮሚቴው ለምክር ቤቱ ከሚያቀርብበት ሠአት ከ30 ደቂቃ በፊት ሊቀርብ ይችላል።

## አንቀጽ 11
## ማሻሻያ ሞሽን ለምክር ቤት ውይይት ስለሚቀርብበት ሁኔታ

1. ማሻሻያ የቀረበበት ጉዳይ ላይ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ማሻሻያ ሞሽን አቅራቢው በአፈጉባኤው ስሙ ተጠርቶ ማሻሻያውን እንዲያቀርብ ሲፈቀድለት ማሻሻያ ሞሽኑን

ከአጭር ማብራሪያ ጋር በንባብ ያሰማል::

2. ማሻሻያው በብዙ አባላት ስም የቀረበ ከሆነ ስሙ በመጀመሪያ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው አባል የ"እኔ-----" ማሻሻያ ተብሎ የተቀመጠው አባል እንዲያቀርብ ይደረጋል::
3. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው አባል የሌለ እንደሆነ ከሌሎቹ ከአቅራቢዎቹ አንዱ እንዲያቀርብ ይደረጋል።
4. ማሻሻያ ለማቅረብ የጠየቀ አባል በአፈጉባኤው ስሙ ሲጠራ በምክር ቤቱ የሌለ እንደሆነ ማሻሻያውን እንደተወ ይቆጠራል::
5. አንድ አባል የማሻሻያ ሞሽን በማቅረቡ ምክንያት ከሌሎች የምክር ቤት አባላት የተለየ የመናገር ዕድል ሊሰጠው አይችልም::
6. የማሻሻያ ሞሽን አቅራቢ የመጨረሻ አስተያየት የመስጠት መብት አይኖረውም::

## <u>አንቀጽ 12</u>

## <u>በማሻሻያ ሞሽን ላይ ስለሚደረግ ውይይት</u>

1. የማሻሻያ ሞሽን ለምክር ቤቱ ውይይት ሲቀርብ በዋናው ሞሽን፣ በረቂቅ ውሳኔው፣ በረቂቅ ህጉ ወይም በኮሚቴ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ይደረግ የነበረው ውይይት ይቆማል::
2. በማሻሻያ ሞሽኑ ላይ የሚደረገው ውይይት ከተጠናቀቀ በኋላ በሌላ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ውይይት ይካሄዳል።
3. ሌላ ማሻሻያ ሞሽን ያልቀረበ ከሆነ ወይም በቀረቡት ማሻሻያ ሞሽኖች ላይ በየተራ ውይይት ከተደረገ በኋላ በዋናው ሞሽን፣ በረቂቅ ውሳኔው በረቂቅ ህጉ ወይም በኮሚቴው ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ውይይቱ ይቀጥላል::
4. ምክር ቤቱ በመጀመሪያ የማሻሻያ ሞሽኑን መቀበሉን ወይም ውድቅ ማድረጉን ከወሰነ በኋላ በመሠረታዊ ሞሽን ላይ ውሳኔ ወይም አስተያየት ይሰጣል::
5. ምክር ቤቱ የማሻሻያ ሞሽኑን ከተቀበለው መሠረታዊ ሞሽን በማሻሻል መቀበሉን በድምጽ ይወስናል::
6. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 4 እና 5 የተደነገገው ቢኖርም ምክር ቤቱ በማሻሻያ ሞሽኑ ላይ ድምጽ ሳይሰጥ በመሠረታዊ ሞሽን ላይ ብቻ ድምጽ የሰጠ እንደሆነ የማሻሻያ ሞሽኑን ውድቅ እንዳደረገው ይቆጠራል::

## <u>አንቀጽ 13</u>

## <u>ማሻሻያ ሞሽን የማቅረብ ሃሳብን ስለመተው</u>

1. የማሻሻያ ሞሽን አቅራቢ ያቀረበውን ማሻሻያ ሊተው ወይም ሊሰርዝ ይችላል:: ሆኖም ማሻሻያው በምክር ቤቱ ውይይት እየተደረገበት ከሆነ በጉዳዩ ላይ የሚደረገው ውይይት ሊቆም የሚችለው በም/ቤቱ ውሳኔ ይሆናል።

2. ንዑስ ማሻሻያ የቀረበበት የማሻሻያ ሞሽን በንዑስ ማሻሻያው ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት መተው አይቻልም፡፡
3. የማሻሻያ ሞሽኑ ከአንድ በላይ በሆኑ አባላት የቀረበ ሆኖ ከአቅራቢዎቹ አንዱ በማሻሻያው ላይ ውይይት እንዲደረግበት ከጠየቀ ውይይት ሊካሄድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 14

## በመሰረታዊ ሞሽንና በረቂቅ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ማሻሻያ ሞሽን

ስለሞሽን አቀራረብ በደንቡ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመሰረታዊ ሞሽንና በረቂቅ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የማሻሻያ ሞሽን ግልጽ፣ ያልተንዛዛና በርካታ ጉዳዮች በአንድ ላይ ያልያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 15

## በረቂቅ ህግ ላይ ስለሚቀርብ ማሻሻያ ሞሽን

በረቂቅ ህግ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ

ሀ/ ረቂቅ ህጉ ለዝርዝር ዕይታ ወደ ኮሚቴ እንዲመራ በቀረበ ሞሽን ላይ፣

ለ/ በረቂቁ ህግ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ፣

ሐ/ በኮሚቴ በቀረበ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ በደንቡ መሰረት ሊቀርብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 16

## ረቂቅ ህግ ወደ ኮሚቴ እንዲመራ ስለሚቀርብ የማሻሻያ ሞሽን

አንድ ረቂቅ ህግ ለዝርዝር ዕይታ ለቋሚ ኮሚቴ እንዲመራ በቀረበ ሞሽን ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ረቂቁ እንዲመራ የሚፈለገውን ኮሚቴ ወይም ኮሚቴዎች በመግለጽ ያለማብራሪያ ወይም አጭር ማብራሪያ ጋር ሊቀርብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 17

## በረቂቅ ህግ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ሞሽን መመዘኛ

1. በደንቡ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በረቂቅ ህጉ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ምክር ቤቱ የተሟላና ግልጽ ውሳኔ ሊያሳልፍ በሚችልበት ሁኔታ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ማሻሻያው የሚካተትበትን ገጽ፣ ምዕራፍ፣ አንቀጽ፣ ፓራግራፍ፣ ዓረፍተ ነገር፣ ሀረግ ወይም ቃል ተጠቅሶና ተለይቶ መቅረብ አለበት፡፡
2. ቀላል ወይም ጥቃቅን ጉዳዮች የያዘ ወይም ትርጉም የለሽ መሆን የለበትም፡፡
3. የረቂቅ አዋጁ አካል ያልሆነውንና ከረቂቁ ጋር ተያይዞ የሚቀርበውን መግለጫ ወይም ማብራሪያ የሚያሻሽል ወይም የሚያርም መሆን የለበትም፡፡
4. የረቂቅ ህጉ ዋና ዓላማ የሚያዛባ ወይም ከታሰበለትዓላማ ውጭ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

## አንቀጽ 18

## በማሻሻያ ረቂቅ ህግ ላይ ስለሚቀርብ ማሻሻያ ሞሽን

ከላይ በአንቀጽ 17 ከተደነገገው በተጨማሪ የነባር አዋጅን የተወሰነ ክፍል ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ሞሽን፣

1. በረቂቁ ላይ በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ መሆን አለበት፡፡
2. በረቂቁ ያልተጠቀሰና በዋናው አዋጅ ላይ የሚገኝ ምዕራፍ አንቀጽ ትርጓሜ ቃል ወይም ሀረግ የሚመለከት መሆን የለበትም፡፡
3. ረቂቁ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ከረቂቁ የተፈጻሚነት ወሰን በማለፍ ለማሻሻል የሚሞከር መሆን የለበትም፡፡

## አንቀጽ 19

## የማሻሻያ ሞሽን ስለማይቀርብበት ሁኔታ

የአለም አቀፍ ስምምነቶችን አንቀጽ ቃል ወይም ሀረግ ለመለወጥ፣ ለመሰረዝ ወይም ለመጨመር የሚቀርብ ማሻሻያ ተቀባይነት የለውም።

## አንቀጽ 20

## ማሻሻያ ሞሽን ለም/ቤቱ ስለሚቀርብበት ሁኔታ

1. አንድ ረቂቅ ህግ ለዝርዝር ዕይታ ወደ ኮሚቴ እንዲመራ የሚቀርብ ማሻሻያ ሞሽን ዋናው ሞሽን እንደቀረበ እጅ በማውጣትና በአፈጉባኤው ሲፈቀድ ወዲያውኑ በቃል መቅረብ አለበት፡፡
2. በቀረበው የማሻሻያ ሞሽን ላይ ምክር ቤቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በረቂቅ ህግ ወይም በኮሚቴ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ዝርዝር ማሻሻያ ያቀረበ አባል ማሻሻያው የቀረበበት ምዕራፍ፣ ክፍል ወይም አንቀጽ ላይ ውይይት በሚደረግበት ወቅት ማሻሻያውን ማቅረብ አለበት፡፡
4. በረቂቅ ህግ ወይም በኮሚቴ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ የቀረበው ማሻሻያ ተቀባይነት ካገኘ ማሻሻያው በረቂቅ ህጉ ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡
5. የቀረበው ማሻሻያ ተቀባይነት ያጣ እንደሆነ ኮሚቴው ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ወይም ያለማሻሻያ እንዲጸድቅ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 21

## ስለ ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን በጠቅላላ

1. የአፈጉባኤውን ፈቃድ ያገኘ ማንኛውም አባል በቀረበ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ሊቀርብ የሚችለው ለም/ቤቱ በቀረበ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ብቻ ነው፡፡
3. ማንኛውም የሞሽን ህግና ልማዳዊ አሰራር በንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 22
## የንኡስ ማሻሻያ ሞሽን መመዘኛ

1. በደንቡና በዚህ መመሪያ ስለማሻሻያ ሞሽን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን፣
   - ሀ/ ከማሻሻያ ሞሽኑ ጋር በቀጥታ አግባብነት ያለው መሆን አለበት::
   - ለ/ የማሻሻያ ሞሽኑን ብቻ ለማሻሻል ያለመ መሆን አለበት::
   - ሐ/ መሠረታዊ ሞሽን የማይነካ መሆን አለበት::
   - መ/ የማሻሻያ ሞሽኑ ወሰን የሚያሰፋ መሆን የለበትም::
   - ሠ/ አዲስና የተለየ ሃሳብ የሚያካትት መሆን የለበትም::
   - ረ/ ማሻሻያ ሞሽኑን ሙሉ በሙሉ ውድቅ የሚያደርግ መሆን የለበትም::
2. ንኡስ ማሻሻያ ሞሽንን የሚያሻሽል ሞሽን ማቅረብ አይቻልም::

## አንቀጽ 23
## ስለ ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን አቀራረብ

1. ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ማስታወቂያ ሳያስፈልገው በቃል ሊቀርብ ይችላል::
2. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም እንዲሻሻል የተፈለገው ጉዳይ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለአፈጉባኤው መቅረብ አለበት::
3. ንኡስ ማሻሻያ ሞሽኑ ከማሻሻያ ሞሽኑ ጋር ተጣጥሞ ሊገባ በሚችል ሁኔታ በጽሁፍ መዘጋጀት አለበት::
4. በአፈጉባኤው ስሙ ሲጠራ ንኡስ ማሻሻያውን ከአጭር ማብራሪያ ጋር ሊያቀርብ ይችላል::
5. ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን በማሻሻያ ሞሽኑ፤ ላይ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ሊቀርብ ይችላል::
6. አባሉ እጁን በማውጣት የአፈጉባኤው ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል::

## አንቀጽ 24
## በንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ስለሚደረግ ውይይት

1. በማሻሻያ ሞሽን ላይ ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ሲቀርብ በማሻሻያ ሞሽኑ ላይ የሚደረገው ውይይት ተቋርጦ በንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ውይይት ይጀመራል::
2. በንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ የሚካሄደው ውይይት በቀረበው የማሻሻያ ሞሽን ላይ ብቻ ያተኮረ መሆን አለበት::
3. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በንኡስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ::

4. አንድ አባል ንኡስ ማሻሻያ ሞሽን በማቅረቡ ምክንያት ከሌሎች አባላት የተለየ የመናገር ዕድል ሊሰጠው አይችልም፡፡
5. የንኡስ ማሻሻያ ሞሽን አቅራቢ የመጨረሻ አስተያየት የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 25**

**መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ከጸደቀበት ከመጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ተሾመ ቶጋ (አምባሳደር)

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት

አፈጉባኤ